

PLAN INTERNATIONAL

# በአቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር መመሪያ



# ምንድነው?

ይህ መመሪያ አቻን መሰረት ላደረጉ የተለያዩ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብሮች አጭር እና ተግባራዊ አጠቃላይ እይታን ይሰጣል- [1]


1. የአቻ ድጋፍ
2. የአቻ አሰሳ
3. የአቻ ትምህርት
4. የአቻ ምክር

አላማው የፕሮግራም ሠራተኞች በፕሮግራሙ ዓላማዎች እና ዐውድ ላይ በመመርኮዝ ተገቢውን በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር/ (ሮች) አይነትን ለመምረጥ እንዲችሉ ለመደገፍ አለው ፡፡የተለያዩ አቻን መሰረት ያደረጉ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብሮች የተለያዩ መጠን ካላቸው ቡድኖች ጋር የሚሰሩ ሲሆን በተለያዩ መንገዶች ድጋፍ ይሰጣሉ ፡፡ እያንዳንዱ መርሃ ግብር አቻዎችን ይጠቀማል ነገር ግን የሚሰሩት ሥራ ብዙውን ጊዜ የተለየ ነው ፡፡

‘አቻ/እኩያ’ ተመሳሳይ ሁኔታዎችን እና ልምዶችን የሚጋሩ እና ድጋፎችን ወይም መመሪያዎችን የሚሰጡ፣ ሰዎችን ይገልጻል። አቻዎች ተመሳሳይ ዕድሜ ሊኖራቸው ይችላል ፣ ወይም ከማሕበረሰቡ የተገለሉ እርጉዝ ወይም ህጻን ልጅ ያላቸውን ወጣት ልጃገረዶችን ባሉ ጉዳዮች ላይ የጋራ ተሞክሮ ሊኖራቸው ይችላል።አቻዎች ብዙውን ጊዜ የበጎ ፈቃደኛ ሠራተኞች ናቸው እንዲሁም ከባለሙያ አካላት ጋር በተለያዩ አካባቢዎች ለምሳሌ ከትምህርት ቤት መምህራን ወይም በጤና እንክብካቤ ሠራተኞች ጋር ተጨማሪ ድጋፍን ለመስጠት ወይም በተለያዩ መንገዶችን ከፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ጋር ለመገናኘት አብረው ይሰራሉ ፡፡

ፕላን ኢንተርናሽናል የአቻ ትምህርትን በጤና ፣ በትምህርት ፣ በጥበቃ እና በሰብዓዊ ሥራዎች ውስጥ በተለያዩ መርሃ ግብሮች እና አውዶች ውስጥ ለብዙ ዓመታት ሲጠቀም ቆይቷል ፡፡ሆኖም ፣ አንዳንድ ጊዜ የአቻዎች ትምህርት ያለ በቂ ትንተና ስለሚመረጥ የፕሮግራሙን የተፈለገውን ውጤት ለማሳካት ውጤታማ መርሃ ግብር ላይሆን ይችላል ፡፡ይህ መመሪያ የመስሪያ ቤቱን ሰራተኞች አቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብርን እንዲመረምሩ፣ ካሉት ሰፊ የመርሃ ግብር አይነቶች እንዲመረጡ እንዲሁም በወጥነት ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲወስዱት ለማረጋገጥ ይረዳል ፡፡

በአቻ ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች የአጠቃላይ ወይም የሰፊ ‹መርሃ ግብር› አንድ አካል ከመሆን በተጨማሪ ‹ራሱን የቻለ መርሃግብር ሆኖ› ተዘጋጅተዋል ፡፡ እያንዳንዳቸው ተመሳሳይ ዓይነት ቅርጸትን ይከተላሉ። ሁሉም ስለ መርሃ ግብሩ ዓላማ ማጠቃለያ መረጃን ፣ አውድ / ቅንብር; የመርሃ ግብሩን ጥቅሞች እና ገደቦች; እና የአተገባበር ምክሮችን ያካትታሉ።ማብራሪያ ምሳሌዎች፣ መተግበሪያ መሳሪያዎች እና ሀብቶች/ሰነዶችም ማጣቀሻንም እንዲሁ ያካትታሉ ፡፡ በዚህ መመሪያ ውስጥ የቀረበው መረጃ የተሟላ ባለመሆኑ እንደ የአውዱ ሁኔታ ተጨማሪ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋሉ



[1] Peer research is another intervention, but not covered within the scope of this guidance.

# ለምን?

- አቻዎች ከሌሎች ጋር ግንኙነቶች ለመገንባት እና ነገሮችን የበለጠ ከራሳቸው ጋር ተዛማጅ ለማድረግ የሚረዱ ቁልፍ የግል ባህሪያትን ፣ ሁኔታዎችን እና / ወይም ልምዶችን ይጋራሉ
- አቻዎች  አዎንታዊ ባህሪዎችን እና አመለካከቶችን ራሳቸውን አርዓያ በማድረግ ያራምዳሉ ፡፡ ወጣቶች የመለወጥ አቅማቸውን እንዲገነዘቡ በመርዳት የታመኑ የመረጃ ምንጮች እንዲሆኑ እና በእውቀት ፣ በአመለካከት እና በውሳኔ አሰጣጥ ለውጦችን መደገፍ ይችላሉ ፡፡
- አቻዎች ለሌሎች ባለሙያዎች የበለጠ ፈታኝ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ለመድረስ ይችላሉ ፡፡ በተለይም በዚህ ዕድሜ እኩያነት/አቻነት በጣም አስፈላጊ ስለሚሆኑ በጉርምስና እድሜ ላይ ያሉትን በማሳተፍ ረገድ ጥሩ አስተዋጻኦ ያደርጋሉ ፡፡
- በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብሮች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የአቻ መርሃ ግብሮች  በእውቀት እና በአመለካከት ፣ በወሊድ መከላከያ እና ኮንዶም አጠቃቀም  እንዲሁም በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ዙሪያ ውሳኔዎችን ለማድረግ በሚያስችል በራስ መተማመን ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ፡፡ ሆኖም  የአቻ መርሃ ግብር እንደ ያልታቀደ እርግዝና ፣ ኤች አይ ቪ እና የአባላዘር በሽታዎች ባሉ የጤና ውጤቶች ዙሪያ ያለውን ተጸእኖ በተመለከተ ያለው ማስረጃ ውስን ነው ፡፡[2,3]
- አቻዎች የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ዙሪያ የሚደረግን ውይይት ፣ እና ውሳኔ አሰጣጥን ይደግፋሉ ፡፡ በተጨማሪም ወጣቶች በአዎንታዊ መንገድ ራስን መቀበል ፣ በራስ መተማመን እንዲኖራቸው እና ለራስ ከፍ ያለ ግምት እንዲያዳብሩ ሊረዱ ይችላሉ።
- አቻዎች እርዳታ የመሻት ባህሪን ያሻሽላሉ እናም የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መረጃ ፣ ሀብቶች እና አገልግሎቶችን ወጣቶች እንዲያገኙ ድልድይ በመሆን ያገለግላሉ ፡

# እንዴት?

- *የመርሃ ግብር መረጣ:* በአንድ ፕሮግራም ውስጥ ለማሳካት እየሞከሩ ያሉትን የተወሰኑ ውጤቶችን ያስቡ፡፡ በአቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች ሥራን ለማሟላት እና ለመደገፍ ሰፋ ያለ የመርሃ ግብር ስርዓት አካል መሆን አለባቸው ፡፡ ይህም ለስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች  በመረጃ እና በራስ መተማመን ላይ ውሳኔዎችን ማድረግ እንዲሁም ለተሟላ ፣ ለወጣቶች ተስማሚ እና ለስርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጭ  የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች አገልግሎቶችን ለማግኘት ጤናማ ውሳኔ አሰጣጥ እና ክህሎቶች ላይ ማተኮር ማለት ነው ፡፡
- *አቻዎችን መመልመል ፡፡* ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያካትት የምልመላ እና የመምረጥ ሂደት ያቋቁሙ። ጥሩ የመግባባት እና የማዳመጥ ችሎታ ያላቸውን ትዕግሥት; ርህራሄ, አክብሮታዊ እና የማይፈረጅ አመለካከቶችን የሚያሳዩትን  አቻወችን ምረጡ
- *ስልጠና:* አቻዎች ሁሉን አቀፍ የመጀመሪያ ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል (እንደ ሁኔታው ከ3-5 ቀናት ) እና መደበኛ የክትትል ሥልጠና ለምሳሌ በየ 6 ወሩ የሚከናወን ይሆናል።፡ስልጠናው  የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ላይ እውቀትን ከማጎልበት እና ሥራቸውን ለማድረስ በሚያስፈልጉት ክህሎቶች ላይ (ይህም እንደ ማመቻቸት ፣ የምክር እና ጥንቃቄ የተሞላባቸው ውይይቶች አያያዝ እና  የደህንነት ጥበቃ) ከማተኮር በተጨማሪ በተለይም ከስርዓተ ፆታ ፣ ስነ ወሲባዊነት ፣ ከጎሳ እና ከእምነት ጋር የተያያዙ  የአቻ አመለካከቶችን መዳሰስ አለበት ፡፡
- *ቁጥጥር:-* _አቻዎች ሥራቸውን በብቃት ለመፈፀም  ከሰለጠነ ባለሙያ ድጋፍ ይፈልጋሉ - ለምሳሌ ፡፡ አስተማሪ ወይም የጤና እንክብካቤ ሠራተኛ ሊሆን ይችላል ፡፡አቻዎች የመወያያ ክፍለ-ጊዜዎች እንዲኖሩዋቸው ፣ አስቸጋሪ ጉዳዮችን ለማስተናግፍድ ድጋፍ ለማድረግ እና የሚፈለጉትን ተጨማሪ ስልጠናዎችን ለመለየት ፣ ወርሃዊ ስብሰባዎች እና የሩብ ዓመቱ ምልከታ እንዲሁም መደበኛ አስተያየት መስጫ ክፍለጊዜዎች እድል ይፍጠሩላቸው ፡፡
- *ሎጂስቲክስ እና ድጋፍ:-* የአቻዎች መልቀቅ በጣም የተለመደ ነው ፡፡ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣ ትራንስፖርት እና  አበልን ለመሸፈን የገንዘብ ድጋፍን ጨምሮ ፣ መክርን እና ቀጣይነት ያለው ሥልጠና አቋርጦ የመውጣት ችግርን ለማስወገድ ይረዳል ፡፡ በአከባቢው በወጣቶች ከሚመራ ድርጅት ጋር አብሮ መሥራትም የበለጠ ዘላቂ መፍትሔ ሊያመጣ ይችላል ፡፡
- *ፋይናንስ:-* አቻን መሰረት ያደረገ መርሃ ግብር በአነስተኛ ወጪ ይተገበራል በመባል ብቻ መመረጥ የለበትም።  የገንዘብ ሀብቶች የሥልጠና ወጪዎችን እና ድጎማዎችን፣ ለመሸፈን በሰራ ወቅት የአቻዎችን ፣ የትራንስፖርት ወጭ ፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች እና ለሌሎች ሥራዎቻቸውኝ ለመደገፍ ገንዘብ ያስፈልጋል ፡፡
- *ቁሳቁሶች:-* በአቻዎች ላይ የተመሠረቱ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች  መርሃ ግብሮችን ወጤታማ ለማድረግ ለመጠቀም ቀላል እና ግልጽ የሆኑ  እንደ ፍላሽ ካርዶችን ፣ ስዕሎች፣ ጥያቄዎች ፣ ቀላል የክፍለ-ጊዜ ዝርዝር መግለጫዎች ፣ እና የፈጠራ እንቅስቃሴዎች እና ጨዋታዎች እንዲሁም የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ቀሳቁሶችን ጨምሮ መጠቀምን ይጠይቃል ።
- *ይዘት:-* ይዘቱ በአቻዎች ለመቅረብ ተገቢ መሆኑን ያረጋግጡ። ከብዙ ሙያዊ ይዘቶች ይልቅ አመለካከቶችን የሚያወያዩ እና ክህሎቶችን የሚያዳብሩ አሳታፊ እንቅስቃሴዎችን የመሳሰሉት በአቻዎች ቢቀርቡ ተገቢ ነው።  ይዘቱ ከፕላን ኢንተርናሽናል እሴቶች እና የተሟላ የስነ ወሲብ ትምህርት ላይ ከሚገኙት የጥራት ደረጃዎች ጋር መጣጣም አለበት።
- *አመቺ ድባብ :-* በአቻዎች ላይ የተመሠረቱ መርሃ ግብር የአቻዎች እሴት/ዋጋ እውቅና በሚሰጥበት አውድ ውስጥ ማቅረብ ያስፈልጋል ፡፡ይህ ማለት በመርሃ ግብር ውስጥ የአቻዎችን ስራ ለመረዳትና ለመደገፍ ከወላጆች ፣ ከመምህራን ፣ ከጤና አጠባበቅ ሰራተኞች እና ከማህበረሰቦች ጋር መተባበር እና  በአቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃግብሮች እንደ ለወጣቶች-ተስማሚ እና  ለስርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ ከሆኑ  የጤና አገልግሎቶች እና ቁሶች ለምሳሌ ኮንዶሞች ጋር የተገናኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡.
- *የደህንነት ጥበቃ:* የአቻዎችን እና የፕሮግራም ተሳታፊዎችን ደህንነት ማረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ፡፡አቻዎች በሥራቸው ውስጥ ጥበቃ የማድረግን አስፈላጊነት መገንዘብ እና  ፣ ጥቃትን በግልጽ መናገር እና ጉዳዮችን ሪፖርት ለማድረግ ፖሊሲዎችን በደንብ ሊያውቁ ይገባል ፡፡ የአቻዎችን የደህንነት አደጋዎች ለመቀነስ እርምጃዎችን ያስቀምጡ - ለምሳሌ. ልዩ ሥልጠናን መስጠት ፣ ራሳቸውን ላለማጋለጥ የምርት ስም የሌላቸውን ቁሳቁሶችን መስጠት እንዲሁም አቻዎች በጥንድ እንዲሠሩ መጠየቅን ሊያካትት ይችላል ፡፡
- *ክትትል እና ግምገማ ፡፡* በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር በፕሮግራሙ ተሳታፊዎች እና አቻዎች ላይ ያለውን ተፅእኖ ለመገንዘብ እና ጥራትን ለማሻሻል ክትትል እና ግምገማ አስፈላጊ ነው ፡፡ መረጃ ከፕሮግራሙ ተሳታፊዎች  ሊሰበሰብ ይችላል።  ይህም መረጃ በእውቀት እና በአመለካከት ላይ  ያሉ ለውጦችን; እንደ  በራስ መተማመን እና ውሳኔ አሰጣጥ ያሉ ክህሎቶች ላይ; እና የእርካታ እና ተሳትፎ ደረጃዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች  ላይ ሊሰበሰብ ይችላል። አቻዎችን በተመለከተ ደግሞ ባዳበሯቸው ክህሎቶች እና ብቃቶች ዙሪያ፣ በፕሮግራሙ ላይ ስላላቸው አስተያየት;  እና ከፕሮግራሙ የመልቀቅ  መጠንን እና ምክንያቶችን በተመለከተ መረጃዎች ሊሰበሰቡ ይችላሉ።



ጠቃሚ ምክር

*አቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር ዲዛይን ፣ ይዘት እና አቅርቦት ጋር የተቆራኙ አደጋዎችን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል የበለጠ መረጃ ለማግኘት “ጉዳት አለማድረስ” የሚለውን መመሪያ ማንበብዎን ያረጋግጡ*

## ንድፈ ሃሳብ እና መረጃ

በአቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች በተፈጥሯቸው የተለያዩ እና የተለያዩ የፕሮግራም ውጤቶችን ለማሳካት በተለያዩ ሁነቶች ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ናቸው ፡፡በዚህ ምክንያት ለአቻ-ተኮር ሥራ የሚሰጠው ማስረጃ በተወሰኑ መርሃ ግብሮች ዙሪያ እና በተወሰኑ የጤና ውጤቶች ዙሪያ ውስን ነው። በተለይም በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያለውን እርግዝና በመቀነስ ፣ [4] ወይም ኤች አይ ቪን ስርጭትን ወይም የአባለዘር በሽታዎችን በመቀነስ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል ፡፡መረጃዎች በአቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች በተናጥል ሲተገበሩ በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ውጤቶች ላይ ውስን ተጽዕኖ እንዳላቸው ያመለክታሉ ፡፡ ስለሆነም በአቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች ለወጣቶች ተስማሚ እና ለስርዓተ ፆታ ምላሽ ሰጭ የሆኑ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች እና አገልግሎቶችን ያካተተ ሰፊ የፕሮግራም አካል ሆነው መተግበር አለባቸው

- ጥናቶች እንደሚያሳዩት በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች እና በኤች.አይ.ቪ ላይ ክፍለ ጊዜዎችን የሚያቀርቡ አቻዎች በኤች አይ ቪ እውቀት ፣ የእርግዝና መከላከያ እና በኮንዶም አጠቃቀም እንዲሁም በወጣቶች የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ዙሪያ ውሳኔዎችን የማድረግ እምነት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል ፡፡

  Sun et al (2016) Assessing Participation and Effectiveness of the Peer-Led Approach in Youth Sexual Health Education: Systematic Review and Meta-Analysis in More Developed Countries. The Journal of Sex Research, Volume 55, 2018 - Issue 1. https://pubmed.ncbi.nlm.nih.gov/27898248/

- የአቻዎች መማከሪያ/የምክር መርሃግብሮች (በቡድን ላይ የተመሰረቱ እና አንድ ለ አንድ) ስለራሳቸው ያላቸው ግምትን በማሻሻል ላይ ፣ የራስን ውጤታማነት እና ማህበራዊ አውታረ መረቦችን በመፍጠር ላይ መሻሻልን አምጥቷል ፡፡በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶችን እና ወጣት ሴቶችን የስነ ተዋልዶ ጤና ዕውቀት እና ባህሪን ለማሻሻል እና የኤችአይቪ አደጋን ለመቀነስ በቡድን ላይ የተመሰረቱ የምክር መርሃግብሮች ከአንድ-ለአንድ ፕሮግራሞች የበለጠ ተፅእኖ አሳይተዋል ፡፡የቡድን መማማሪያ እንዲሁም በትምህርት ውጤት ፣ ገንዘብን በአግባቡ የመጠቀም ጠባይ እና የአመፅ ልምዶች በመቀነስ ዙሪያ መሻሻልን አሳይቷል

  Plourde K, et al (2017) Mentoring Interventions and the Impact of Protective Assets on the Reproductive Health of Adolescent Girls and Young Women. Journal of adolescent health, issue 61. https://pubmed.ncbi.nlm.nih.gov/28528208/

- የአቻዎች ትምህርት በአቻዎች በራሳቸው ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ አለው ፣ ዕውቀት እና ክህሎቶች ይዳብርላቸዋል እንዲሁም የስኬት መነሳሳት ስሜታቸው ላይ እና ለራሳቸው የተሻሻለ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ አወንታዊ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ

  Douglas et al (2018) Reported outcomes for young people who mentor their peers: a literature review. Mental Health Practice 21,9 https://journals.rcni.com/mental-health-practice/evidence-and-practice/reported-outcomes-for-young-people-who-mentor-their-peers-a-literature-review-mhp.2018.e1328/print/abs

- የአቻዎች ድጋፍ ሰዎችን የበለጠ ዕውቀት ፣ በራስ መተማመን እና ደስተኛ እንዲሆኑ ፣ የተገለሉ እና ብቸኛ የመሆንን ስሜቶችን ያቃልላል። ይህም የረጅም ጊዜ የአካል እና የአእምሮ ጤንነት ሁኔታ ላላቸው ሰዎች ጤና እና ደህንንነት ላይ ከፍተኛ መሻሻል እንዲያመጡ ሊያደርግ ይችላል ፡፡ በተለላዩ ጽሁፎች በተደረገው ግምገማ አማካይነት የተለዩ በጣም ተስፋ ሰጭ የሆኑ የአቻ ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ። 1) በስሜታዊ ድጋፍ ላይ የሚያተኩሩ በሰለጠኑ አቻዎች የሚካሄዱ የፊት-ለፊት ቡድኖች; 2) ፊት ለፊት ወይም በስልክ የሚቀርብ አንድ ለአንድ ድጋፍ; 3) በበይነ መረብ ላይ ያሉ መድረኮች; 4) በመደበኛነት (እንደ በየሳምንታዊ) ከሦስት እስከ ስድስት ወር የሚሰጥ ድጋፍ

  NESTA (2015) Peer Support: What is it and does it work? https://www.nationalvoices.org.uk/publications/our-publications/peer-support

- በመረጃዎች ላይ የተደረገው ግምገማ እንደሚያሳየው በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ የሚከሰቱ እርግዝናን ለመቀነስ ፣ ወይም ኤችአይቪን ጨምሮ የአባለዘር በሽታዎችን ስርጭት ለመቀነስ በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር ውስን ተጽዕኖ አሳይቷል

  Chandra-Mouli (2015) What does not work in adolescent sexual and reproductive health: A review of evidence of commonly accepted as best practice. GHSP, Sep 2015. https://www.ghspjournal.org/content/3/3/333.abstract

- ተጨማሪ ስልታዊ ግምገማ እንደሚያሳየው እንደ አንድ መርሃ ግብር የሚተገበር የአቻዎች ማመቻቸት የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ውጤቶች ላይ ውስን ተጽዕኖ እንዳሳደረ አሳይቷል ፡፡ስነ ወሲባዊነትን የሚጎዱ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ምክንያቶች ያላቸውን ስፋት እና ጥንካሬን ስናይ እና የስነወሲብ እና የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ስንመለከት የሚያስደንቅ አይደለም ፡፡

  Rose-Clarke K, Bentley A, Marston C, Prost A (2019) Peer-facilitated community-based interventions for adolescent health in low- and middle-income countries: A systematic review. PLoS ONE 14(1): e0210468. https://doi.org/10.1371/journal.pone.0210468

## ለበለጠ መረጃ ስልቶች እና ስልቶች

- My Peer Toolkit – Western Australia Centre for Health Promotion Research (2010). http://mypeer.org.au/
- Youth power website (various resources). https://www.youthpower.org/
- Using peers to improve sexual and reproductive health and rights of young people living with HIV in Uganda: findings from a Link Up evaluation – Population Council ( 2016). https://www.popcouncil.org/uploads/pdfs/2016HIV_LinkUp_UgandaEndlineBrief.pdf
- Evidence and Promising practices from Peer-Based Approaches in Youth Programmes – USAID, PEPFAR and Youth Power. https://www.youthpower.org/sites/default/files/YouthPower/files/resources/Peer%20Based%20Youth%20Brief%20final.pdf

[2] Medley A, et al.(2009) Effectiveness of peer education interventions for HIV prevention in developing countries: A systematic review and meta-analysis, AIDS Education Prevention, 2009, vol. 21 (pg. 181-206)

[3] Sun et al (2016) Assessing Participation and Effectiveness of the Peer-Led Approach in Youth Sexual Health Education: Systematic Review and Meta-Analysis in More Developed Countries. The Journal of Sex Research Volume 55, 2018 - Issue 1

[4] Chandra-Mouli (2015) What does not work in adolescent sexual and reproductive health: A review of evidence of commonly accepted as best practice GHSP Sep 2015


PLAN INTERNATIONAL
GIRLS GET EQUAL


# ማውጫ

የአቻ ድጋፍ



ገጽ 8

የአቻ አሰሳ



ገጽ 10

የአቻ ትምህርት



ገጽ 12

የአቻ ምክር



ገጽ 14

# የአቻ ድጋፍ




## ምሳሌ

ፍሬድ የተገለሉ ወጣቶችን የሚደግፍ ድርጅት ውስጥ የአቻ ደጋፊ ነው ፡፡አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በማኅበረሰቦች ውስጥ ከወጣቶች ጋር በጥያቄዎቻቸው ላይ በመወያየት ነው ፡፡እሱ ወጣቶችን ተጉዞ ማግኘት ይችል ዘንድ ብስክሌት ተሰጥቶታል እናም ወጣቶች እራሳቸውን ለማግኘት የማይችሏቸውን ኮንዶሞችን እና የወሲብ ማሳለጫ ቅባቶችን ያሰራጫል ፤ የአባላዘር በሽታ እና የኤች አይ ቪ ምርመራዎችን ያካሂዳል ፡፡እንዲሁም የተገለሉ ወጣቶች የተቀየሱ የመረጃ፣ ትምህርት አና መግባቢያ ቁሳቁሶችን ያካፍላል

በፍሬድ ማህበረሰብ ውስጥ ወሲባዊነት እና የወሲብ ጤንነት አሳሳቢ ርዕሰ ጉዳዮች እንደመሆናቸው መጠን ስለራሱ ደህንነት ፣ስለ ደህንነት ጥበቃ ጉዳዮች፣ ስለግላዊነት እና ምስጢራዊነትን ስለመጠበቅ እና ከማህበረሰቡ የሚመጣውን ማንኛውንም ተቃውሞ ወይም አፀፋዊ ስሜት እንዴት መቋቋም እንደሚቻል ያገኘው ስልጠና እንዲያስብ ረድቶታል ፡፡ በተጨማሪም የፕሮግራሙን ተሳታፊዎች በመረጃ እና በቁሳቁስ ለመደገፍ የሚያስችሉ መንገዶችን አካቷል ፡፡ፍሬድ ከሌሎች የአቻዎች ደጋፊዎች ጋር ተግዳሮቶችን ለመጋራት እና የሥራውን ጥራት ለማሻሻል በየወሩ የቁጥጥር ስብሰባዎች ላይም ይሳተፋል ፤ የፍሬድ ተቆጣጣሪ የድንገተኛ/አደጋ ተጠሪዎችን እና ድጋፍን ይሰጠዋል ፡፡ተቆጣጣሪው በተጨማሪ በየሶስት እና አራት ወሩ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰሩትን ስራዎች በመጎብኘት ይመለከታል እንዲሁም አዎንታዊ ግብረመልሶች እና አስተያየቶችን ይሰጣል ፡

ሰዎችን በቀላሉ ለመላክ እንዲችል ፍሬድ በአካባቢያዊ የሚገኙ አገልግሎቶች ማጣቀሻ ቅጾች እና መረጃዎች አሉት ፡፡የሚሰጡት አገልግሎት ለአፍላ ወጣቶችና ስርአተ ፆታን ያማከሉ እንዲሆኑ በሁለት የአከባቢ ጤና ክሊኒኮች ሰራተኞችን ስልጠና ለመስጠት ረድቷል ፡፡አንዳንድ ጊዜ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን የሚጋፈጡ ሌሎች ሰዎችን የሚያገኙበትን አስተማማኝ ቦታ ለመፍጠር የድጋፍ ቡድን ስብሰባዎችን ያመቻቻል ፡፡

## አላማ

- የእኩዮቻቸውን የጋራ ልምዶች በመጠቀም ወጣቶችን ለመደገፍ እና የጤንነት እና የደህንነት ውጤቶችን ለማሻሻል ፡፡
- የተወሰኑ ተግዳሮቶች ወይም ችግሮች ለሚገጥሟቸው ወጣቶች የመቋቋም ችሎታዎቻቸውን ለማዳበር ተግባራዊ እና ስሜታዊ ድጋፍ ለመስጠት ፡

## አውድ/ሁነት

- የአቻዎች ድጋፍ በተለያዩ ቅንብሮች/ሁኔታዎች ለምሳሌ በቤቶችን ፣ በማህበረሰብ ቦታዎችን ፣ በጤና ተቋማትን፣ በወጣት ክበቦችን ላይ ሊሰጥ ይችላለ። በተጨማሪም በእርዳታ መስመሮች ፣ በበይነ መረብ ላይ ባሉ የድጋፍ ቡድኖች ፣ በማህበራዊ አውታረመረቦች እና / ወይም በድረ-ገጾች በርቀት መድረስ ይቻላል ፡፡ በ 1 ለ 1 ወይም በቡድን መርሃ ግብርም ሊሰጥ ይችላል

## ጥቅሞች::

- የአቻዎች ድጋፍ የረጅም ጊዜ የአካል እና የአእምሮ የጤንነት ችግር ላላቸው ሰዎች በተለያዩ የጤና እና የድህንነት ውጤቶች ላይ ከፍተኛ መሻሻል ያስከትላል ፡፡
- ከጤና ጋር የተዛመዱ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በተመለከተ አጠቃላይ ድጋፍ ለመስጠት የአቻዎች ድጋፍ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ፣ ለምሳሌ በኤች አይ ቪ የተያዘን ሰው ለመደገፍ እና እንደ የአባላዘር በሽታን ፣ የማህጸን ጫፍ ካንሰር ያሉ የ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጉዳዮችን ለመመርመር እና ማንኛውንም ሪፈራል/ማጣቀሻ ድጋፍል ለማድረግ ይረዳል ፡፡
- የአቻዎች ድጋፍ በ 1 ለ1 ለግለሰብ አግባብ የሆኑ ግላዊ ድጋፍ ለመስጠት ወይም በትንሽ ቡድኖች ውስጥ መጠቀም ይቻላል ፡፡

## ተግዳሮቶች / ውስንነቶች::

- የአቻ ድጋፍ መርሃግብሮች ከሌሎች አቻ ላይ መሰረት ካደረጉ መርሃ ግብሮች የበለጠ አቻወችን መመልመል ያስፈልጋቸዋል ምክንያቱም የአቻዎች ድጋፍ ብዙውን ጊዜ ለረጅም ጊዜ በመደበኛ ሁኔታ 1 ለ 1 ግንኙነቶች ላይ የተመሠረተ ነው ፡፡የአቻ ደጋፊዎች ለደንበኞቻቸው ምላሽ የሚሰጡ እና እንዳስፈላጊነቱ ተለዋዋጭ እና ተደራሽ መሆን አለባቸው ፡፡
- የአቻ ደጋፊዎች ብዙ ጉዳዮችን ማስተዳደር ቢችሉም ከፍተኛ ድካምን ለማስቀረት ቀጣይነት ያለው አማካሪ ፣ ድጋፍ ፣ ምክር እና ክትትል ያስፈልጋቸዋል ፡፡ብዙውን ጊዜ በራሳቸው ድህንነት ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ለወጣቶች ድጋፍ ይሰጣሉ ፡፡
- የአቻ ደጋፊዎች የተለያዩ ጉዳዮችን በበላይነት ለመቆጣጠር ሊፈልጉ ይችላሉ። ስለዚህ አቻዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል።ውጤታማ ሪፈራል/የማጣቀሻ አገልግሎት ለማድረግ የአካባቢ አገልግሎቶችን እና የድጋፍ ድርጅቶችን በተመለከተ ጥሩ ዕውቀት ሊኖራቸው ይገባል ፡፡ ለምሳሌ ፣ በኤች አይ ቪ ላይ ድጋፍ ያለው ሰው በቤተሰብ ፣ በአእምሮ ጤንነት ወይም ግንኙነቶች እና በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ ከአቻ ደጋፊው እርዳታ ይፈልግ ይሆናል ፡፡
- የአቻ ደጋፊዎች የሰለጠኑ ባለሙያዎች አይደሉም ፡፡ በእነሱ ላይ የተቀመጡ ተስፋዎች ተጨባጭ መሆን እና
- ፕሮግራሞቹ የባለሙያ ድጋፍ እንዳላቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል ፡፡

## አተገባበር:

- ከፕሮግራም ተሳታፊዎች ጋር ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸውን እና ተግዳሮቶችን ከሚረዱ እና ርህራሄን ማሳየት የሚችሉ እኩያዎችን ይምረጡ
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ስልጠና ከመስጠት በተጨማሪ አቻዎችን በማማከር ችሎታ ላይ ስልጠና ይሰጡ ፡፡
- ተገቢውን ካሳ/ክፍያ ለመወሰን አጠቃላይ ግምገማ ያካሂዱ ፡፡[5]
- የአቻ ደጋፊዎች በፕሮግራሙ ተሳታፊዎች እና አቻዎች ዙሪያ የሙያ ድጋፍን ከሚያደርጉ እና ከሚመለከታቸው (በወጣቶች የሚመሩ ወይም በጎልማሳዎች በሚመሩ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በመሚያካትቱ አጠቃላይ የድጋፍ ስርዓት ውስጥ መስራታቸውን ያረጋግጡ ፡፡ከተለያዩ ተዛማጅ አገልግሎቶች ለምሳሌ የምክር ፣ የህግ ፣ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች አገልግሎቶች እና የሸቀጥ አቅርቦቶች ጋር ተጨማሪ ትስስር ሊኖር ይገባል ፡፡
- የአቻ ደጋፊዎች ከፕሮግራም ተሳታፊዎች ጋር እምነት የሚጣልባቸው ግንኙነቶችን ለማዳበር ጊዜ እንደሚፈልጉ እውቅና መስጠት ያስፈልጋል።የስሜታዊ ድጋፍ መተማመንን ፣ ግልፅ ውይይትን እና ለፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት በተሻለ አንድ-ለአንድ ወይም ከአምስት እስከ ስምንት ተሳታፊዎችን በሚይዙ አነስተኛ ቡድኖች ሊሰጥ ይችላል ፡፡ የመረጃ ክፍለ ጊዜዎች ከ 12 እስከ 15 ተሳታፊዎችን በሚይዙ ትላልቅ ቡድኖች ሊሰጡ ይችላሉ ፡፡
- በጣም ተስፋ ሰጪ የሆኑት የአቻ ድጋፍ ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ: [6]
  - » በሰለጠኑ እኩዮች የሚሰጡ ፣በስሜታዊ ድጋፍ፣ ልምዶችን በማካፈል ፣ በተግባራዊ እንቅስቃሴዎች እና በትምህርት ላይ ባተኮሩ የፊት-ለፊት ቡድኖች የሚካሄዱ
  - » አንድ ለአንድ የሚደረግ ድጋፍ ፊት ለፊት ወይም በስልክ የሚሰጥ
  - » በበይነ መረብ መድረኮች ላይ በተለይም ዕውቀትን እና ጭንቀትን ለማሻሻል
  - » በመደበኛነት (ለምሳሌ እንደ በየሳምንቱ የሚሰጥ) ከሦስት እስከ ስድስት ወር ድረስ የሚሰጥ ድጋፍ

## ለበለጠ መረጃ ስልቶች እና ስልቶች:


- NESTA (2015). Peer support: What is it and how does it work? https://www.nationalvoices.org.uk/sites/default/files/public/publications/peer_support_-_what_is_it_and_does_it_work.pdf
- NESTA (2016): The power of peer support. https://media.nesta.org.uk/documents/cfsaif_power_of_peer_support.pdf


[5] Plan International (2021) A Recommended Framework for Volunteerism and Compensation for Young People.
[6] NESTA, (2015). Peer Support: What is it and does it work? (see Tools & Resources)

# የአቻ አሰሳ




## ምሳሌ

ናዲያ የኤች አይ ቪ ህክምና እና እንክብካቤን በሚሰጥ ክሊኒክ ውስጥ የእኩያ አሳሽ ነች ፡፡በኤች አይ ቪ የተያዙ ወጣቶችን ትደግፋለች። በክሊኒኩ ስርዓት ውስጥ ታግዛቸዋለች ፡፡ ናዲያ በክሊኒኩ ውስጥ በክሊኒኩ ቡድን የተላኩ ወጣቶች የምታገኝበት አነስተኛ ክፍል አላት ፡፡በክሊኒኩ ውስጥ ለኤችአይቪ አማካሪዎች ተጨማሪ ድጋፍን ታቀርባለች ፣ ወጣቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር ፣ ጭንቀታቸውን በማዳመጥ እና ስለ ኤች አይ ቪ ሕክምና የተለያዩ ደረጃዎች መረጃ ትሰጣቸዋለች ፡፡ ክሊኒኩ በሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች ላይም መረጃ ታጋራለች ፡፡

ናዲያ በክሊኒኩ ውስጥ የቡድኑ አካል ስትሆን በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ደንበኞች የጉዳይ አስተዳደር ስብሰባዎች ላይ ትሳተፋለች ፡፡ በራሷ ግንኙነቶች ላይ የተመሠረተ መረጃን ትሰጣለች። ከፀረ ኤች አይ ቪ-ቫይረስ ሕክምና አጠቃቀም ጋር ተያያዥነት ያሉ ጉዳዮችን ታነሳለች። ከቤተሰብ ሁኔታ ፣ ከአእምሮ ጤንነት ወዘተ ጋር የተዛመዱ ማናቸውንም ስጋቶች ታነሳለች። ለህክምና ምዝገባ መረጃዎች አስተዋፅዖ ታደርጋለች ፡፡ናዲያ በተጨማሪም ደንበኞቿን ከሐኪም ወይም ነርስ ጋር ቀጠሮ ሲኖራቸው አብራ ትሄዳለች ፣ መድሃኒቶቻቸውን እንዲወስዱ ትረዳቸዋለች፤ ስላላቸው ቀጠሮዎችም ታስታውሳቸዋል ፡፡አንዳንድ ጊዜ ናዲያ በክሊኒኩ ውስጥ ላሉት ወጣቶች የመረጃ ስብሰባዎችን እና የድጋፍ ቡድኖችንም ታካሂዳለች ፡፡

## ዓላማ

- የሰዎችን ግንዛቤን በማሳደግ ፣ ለምሳሌ በጤና እንክብካቤ  እና ሕጋዊ ስርዓቶች ውስጥ መምራት እና በሂወት ጉዞአቸው ላይ አብረዋቸው መጓዝ  ፡፡የአቻዎች አሰሳ የአቻዎች ድጋፍ ሚና ዝርፍ ሲሆን ፣ በጤና አጠባበቅ ስርዓት ወይም ተቋም ውስጥ ይገኛል ፡፡የአቻ አሳሾች ከራሳቸው ተሞክሮ በመነሳት  አሰራሮችን ለማብራራት ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለማጉላት እና ዋስትና ለመስጠት ይሰራሉ ፡፡
- የፕሮግራም ተሳታፊዎች ውሳኔ አሰጣጥ ክህሎቶችን ፣በራስ የመተማመን እና ስርዓትንና መብቶችን የመረዳት ችሎታዎችን ለመገንባት።
- በፕሮግራሙ ተሳታፊዎች እና በአገልግሎት ሰጭዎች መካከል ግንኙነቶችን ለማጠናከር ፡፡

## ዐውድ እና / ሁነቶች

- የአቻዎች አሰሳ በጤና ክሊኒኮች እና በሆስፒታሎች የሚሰጥ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ 1 ለ 1 ይሰጣል ፡፡
- የአቻ አሳሾች የጉዳዩ አስተዳደር ቡድን አካል ሆነው በጤና አጠባበቅ ስርዓት ውስጥ ተካትተዋል ፡፡እነሱ በተቋሙ ውስጥ ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ሊቀመጡ ይችላሉ። ጊዜያቸውንም በጤና ተቋሙ ወስጥ ያሳልፋሉ

## ጥቅሞች:

- የአቻ አሳሾች እንክብካቤን በቀጣይነትን የሚደግፉ ሙያ ቀመስ ባለሞያዎች ናቸው ፡፡እነዚህ አቻዎች ሰዎች በስርዓቱ ውስጥ እንዲቆዩ ፣ በመንገዳቸው ላይ ተጓዳኝ በመሆን ፣ ቁልፍ እርምጃዎች እንዲከተሉ በማረጋገጥ እና በክትትል ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመቀነስ ሊረዱ ይችላሉ
- የአቻ አሳሾች ወጣቶች ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚገለሉባቸውን ስርዓቶች ይረዳሉ ለምሳሌ የተገለሉወጣቶች ፣  ጎሳዎች በጤና ሥርዓቶች ውስጥ ያሉ ወጣቶችን ያካትታል ፡፡
- አቻ አሳሾች ለወጣት ደንበኞቻቸውን ጥብቅና በመቆም ለእነሱ ድምጽ ሊሆኑ ይችላሉ

## ተግዳሮቶች / ገደቦች

- አቻ አሳሾች ስለ ተፈላጊ ተቋማት እና ማህበረሰብ-ተኮር አገልግሎቶች የባለሙያ ዕውቀት ይፈልጋሉ። ለደንበኞቻቸው ስላሉ እና ስለ ሥርዓቱ ሂደቶች እና ፕሮቶኮሎች ጥልቅ ግንዛቤ ያስፈልጋቸዋል ፡፡
- የአቻ አሳሾች በአገልግሎት አቅራቢዎች ቡድን ወይም በጉዳይ አስተዳደር ቡድን ውስጥ መካተት አለባቸው ፡፡እነሱ በጤና እንክብካቤ ቡድኖች እምነት ሊጣልባቸው እና ዋጋ ሊሰጣቸው ይገባል አለበላዚያ ውስን ተጽዕኖ ብቻ ይኖራቸዋል።
- የአቻ አሳሾች ከግል ልምዳችቸው ላይ ስለሚነሱ የባለሙያ ድንበሮችን መጠበቅ አስፈላጊ ነው እና ምን ያህል ማካፈል እንዳለባቸው ማወቃቸው አስፈላጊ ነው ፡፡

## አተገባበር

- የስርዓቱን ሂደቶች እና ፕሮቶኮሎች ለማብራራት እና ለማሰስ እንዲረዱ የተወሰነ የጤና አገልግሎት ወይም የማጣቀሻ/ሪፈራል መንገድን በተመለከተ ቀጥተኛ ልምድ ያላቸውን የአቻ አሳሾችን ይምረጡ።
- የአቻ አሳሾች በጉዳዩ አስተዳደር ቡድን ውስጥ በግልጽ የተቀመጡ ሚናዎች እና ሀላፊነቶች እንዳላቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እንዲሁም ሌሎች አገልግሎት ሰጭዎች የአቻ አሳሾች  ሰዎች በስርዓቱ ውስጥ እንዲቆዩ እና በክትትል ላይ የሚደርሰውን ኪሳራ ለመቀነስ የሚሰሩትን ስራ ዋጋ መረዳታቸውን ያረጋግጡ ፡፡
- የጉዳይ አስተዳደር ቡድን አካል ሆነው በብቃት የመሥራት በራስ መተማመን  እና ችሎታ ያላቸውን እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ 18 እስከ 24 ዓመት የሆኑ የአቻ አሳሾችን ይመልምሉ። በተጨማሪም ወጣቶች ከእነሱ ጋር ጥሩ ግንኙነት መመስረት መቻላቸውን ያረጋግጡ ፡፡

## ለበለጠ መረጃ ስልቶች እና ስልቶች


- Peer Navigation Training Core Modules. FHI 360 (2017) https://www.fhi360.org/sites/default/files/media/documents/resource-linkages-peer-navigation-facilitators-guide.pdf
- Practice Guidelines in Peer Navigation for People Living with HIV. Canadian AIDS Treatment Information Exchange [CATIE] (2018) https://www.catie.ca/ga-pdf.php?file=sites/default/files/practice-guidelines-peer-nav-en-02082018.pdf
- Practice Guidelines: Summary of Recommendations. Canadian AIDS Treatment Information Exchange [CATIE] (2018) https://www.catie.ca/sites/default/files/practice%20guidelines%20EN%20summary%202018%2002%2012.pdf

# የአቻ ትምህርት




## ምሳሌ

በማህበራዊ ግንኙነቶች እና የስነ ወሲብ ጤና ላይ የሚደረጉ ክፍለ ጊዜዎችን ጨምሮ በጤና እና በሕይወት ክህሎቶች ላይ ያተኮረ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክበብን ለመደገፍ አሚር በትምህርት ቤቱ ከስድስት የአቻ አስተማሪዎች አንዱ ሆኖ ተመርጧል ፡፡አሚር ከወጣት ተማሪዎች ጋር የቡድን ስብሰባዎችን እንዴት ማመቻቸት እንደሚቻል፣ውይይቶችን ስለመምራት ፣ አሳታፊ ተግባራትን ስለማዘጋጀት እና ፈታኝ ጥያቄዎችን ስለማስተናገድ የ3 ቀናት ስልጠና ወስዷል ፡፡ እሱ እና ሌሎች የአቻ አስተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ውስጥ የስነ ወሲብ ሥርዓተ-ትምህርትን በሚያስተምር የሳይንስ መምህር ይደገፋሉ ፡፡አስተማሪው አሚር ለክለቡ ክፍለ-ጊዜዎችን እንዲዘጋጅ ይረዳዋል። እንዲሁም አሚር በሚያጋራቸው ርዕሶች እና መረጃዎች ላይም ይነጋገራሉ ፡፡ አሚር በቡድኑ ውስጥ አሳታፊ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ የሚያግዙ ቁሳቀሶች እና የቡድን ጨዋታዎች ዝግጅት ሲኖረው ክፍለ ጊዜዎችን እንዲያቀርብ የሚረዳ መመሪያም አለው ፡፡በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ ላይ እርግጠኛ ካልሆነ አስተማሪውን ለእርዳታ መጠየቅ እንደሚችል ያውቃል ፡፡ ከእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ በኋላ ከአስተማሪው ግብረመልስ ያገኛል እናም ስለገጠመው ማንኛውም ነገር መጠየቅ ይችላል ፡፡አሚር ከተማሪዎች ጋር ጥሩ ግንኙነቶችን ይገነባል። ተማሪዎች ማንኛውም ጥያቄ ካላቸው ለመመለስ በትምህርት ሰዓት ይገኛል።

## ዓላማ

- አቻዎች በቡድን ውይይቶች እና እንቅስቃሴዎች አማካኝነት ለአቻ ተሳታፊዎች የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ላይ ዕውቀትን እና መረጃን ለማካፈል ፡፡
- የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶችን መሠረት ባደረጉ እሴቶች እና አመለካከቶች ላይ ለማንፀባረቅ ፣ ለምሳሌ ስርዓተ ፆታ ፣ ፆታ ፣ ስነ ወሲባዊነት ፣ ግንኙነቶች ፣ ስምምነት እና መከባበርን እና እኩልነትን በማበረታታት ረገድ።
- ከስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጋር በተያያዘ የውሳኔ አሰጣጥ ፣ በድፍረት መግባባት ፣ እና የመደራደርን ችሎትታዎች በተመለከተ የወጣቶችን ችሎታ ለመገንባት።

## አውድ / ሁነቶች

- የአቻዎች ትምህርት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሊተገበር ይችላል ፣ ብዙውን ጊዜ ትምህርት ቤቶች ፣ ኮሌጆች ፣ የወጣት ክበባት ፣ አብያተ ክርስቲያናት ፣ የምሽት ክለቦች ፣ ክሊኒኮች እና / ወይም በማህበረሰብ ቲያትር በኩል ሊሆን ይችላል ፡፡
- የአቻዎች ትምህርት ከቡድኖች ጋር የሚተገበር ሲሆን በትምህርት ቤትም ላይ የተመሠረተ ነው። በምሳ ሰዓት ወይም ከት / ቤት በኋላ ክለቦች ሊተገበር ይችላል

## ጥቅሞች:

- የአቻ አስተማሪዎች ወጣቶችን ‹በእውነተኛ ህይወት› ሁኔታዎች ላይ በመወያየት ከስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ጋር በተያያዘ ያላቸውን አስተያየት እንዲቀይሩ እና እንዲያንፀባርቁ ሊረዷቸው ይችላሉ ፡፡
- የአቻ አስተማሪዎች የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶችን የሚደግፉ አቅም መገንባት ይችላሉ ፣ ለምሳሌ የራስ ውጤታማነትን ፣ የውሳኔ አሰጣጥን ፣ የግንኙነትን ፣ የቁርጠኝነት ስሜት እና ጤናን የመፈለግ ባህርያትን የመሳሰሉትን
- የአቻ አስተማሪዎች መረጃን በማቅረብ እና ወጣቶችን አከባቢያቸው ወዳሉ የድጋፍ አገልግሎቶች በመጠቆም  የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች እና ለሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን ሪፈራል መደገፍ ይችላሉ ፡፡
- አቻ አስተማሪዎች በአንጻራዊነት ትልቅ ከሆኑ ቡድኖች ጋር ለተወሰነ ጊዜ በመስራት ብዙ ወጣቶችን ማግኘት ይችላሉ ፡፡
- የአቻ ትምህርት መርሃ ግብሮች ለአቻ አስተማሪዎች በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ዙሪያ አዎንታዊ ባህሪያትን ለማሳደግ እና በራስ የመተማመን ስሜትን እና አዎንታዊ ስሜቶችን በመፍትጠር ረገድ የተረጋገጡ ጥቅሞች አሏቸው ፡፡

## ተግዳሮቶች / ውስንነቶች

- የአቻ ትምህርት ብዙውን ጊዜ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ አይተገበርም። በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር የሚፈለጉትን ዓላማዎች ለማሳካት  ውጤታማ መርሃ ግብር መሆን አለመሆኑን በተመለከተ በቂ የሆነ  ትንታኔ ሳይደረግ መርሃ ግብሩ ሊሰጥ ይችላል ፡፡
- • የአቻ አስተማሪዎች በቂ ያልሆነ ሥልጠና ፣ ድጋፍ እና ቁጥጥር ሳያገኙ; እና በቂ ባልሆኑ ሀብቶች (ለምሳሌ ድጎማዎች ፣ ሥርዓተ-ትምህርቶች ፣ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች)  ተገቢ ያልሆነ እና ከፍተኛ ሙያዊ ይዘት እንዲያቀርቡ ሊጠበቅ ይችላል ፤ ፡፡
- የአቻ አስተማሪዎች ተገቢ ያልሆነ እና ትምህርት ለመስጥት ሙሉ ዝግጁ ባልሆኑባቸው እና በርካታ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ሙያዊ ይዘቶችን ለማቅረብ እና  የመምህራንን ሚና እንዲወጡ ሊጠበቅ ይችላል። ይህም የተሳሳቱ መልዕክቶች እንዲሰራጩ እድልን ይፈጥራል ፡፡
- የአቻ አስተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ብዙ ቁጥርን ከሚይዙ ትላልቅ ቡድኖች ጋር ይሰራሉ ፣ ይህም ግለሰቦችን ለማወቅ እና ትምህርታቸውን / እድገታቸውን ለመከታተል አስቸጋሪ ያደርገዋል ፡፡
- የአቻ ትምህርት የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ውጤቶችን በተናጥል ሲሰጥ ውስን ተጽዕኖ ይኖረዋል። ለምሳሌ በጉርምስና  ጊዜ የሚከሰት እርግዝናን በመቀነስ ፣ ወይም ኤችአይቪን ጨምሮ የአባለዘር በሽታዎችን  ስርጭትን በመቀነስ ዙሪያ በተናጠል ሲሰጥ ውጤቱ አነስተኛ ይሆናል። ስለዚህም እንደ መርሃግብር ከሌሎች መሰል መርሃ ግብሮች ጋር  በመካተት መቅረብ አለበት


## አተገባበር፡

- የአቻ ሥርዓተ-ትምህርትን ፣ መረጃ፣ ትምህርት እና መግባባት ላይ ወይም ቲያትር/ጭውውት ላይ የተመሠረተ ትምህርት መስጠት ይችላሉ ፡፡
- የአቻ አስተማሪዎች  በአዋቂ ተባባሪ አስተባባሪነት ከ15-20 ወጣቶችን ከያዙ ቡድኖችን በጋር በመሆን ጥንድ ሆነው መሥራት ይችላሉ ፤ ትልልቅ ቡድኖች ለመምራት አስቸጋሪ ናቸው ፡፡
- የአቻ አስተማሪዎች ወጣቶች ስለ ወሲብ እና ግንኙነት ፣ አደጋን ስለመገምገም እና በራስ ስለመተማመንን እንዲሁም ውሳኔን ለመወሰን የሚረዱ ክህሎቶችን በማዳበር ዙሪያ ስላላቸው አመለካከት እና እምነት እንዲያስቡ የሚረዱ ተግባራትን ማድረስ አለባቸው  ፡፡ እንደ ስምምነት እና የወጣቶች መብቶች ዙሪያ ያሉ ጉዳዮች ሙያዊ ይዘት ያላቸውን ጉዳዮች ከማቅረብ ይልቅ የበለጠ ተገቢ ናቸው ፡፡

## ለበለጠ መረጃ ስልቶች እና ስልቶች

- Gender Roles, Equality and Transformation (GREAT) Project (Institute for Reproductive Health, Georgetown University, Save the Children, Pathfinder International) has a range of useful resources:
  - » GREAT Activity Cards for very young adolescents https://www.thecompassforsbc.org/project-examples/great-activity-cards-very-young-adolescents
  - » GREAT Activity Cards for older adolescents https://www.thecompassforsbc.org/project-examples/great-activity-cards-older-adolescents
  - » GREAT Activity Cards for married/parenting adolescents https://www.thecompassforsbc.org/project-examples/great-activity-cards-marriedparenting-adolescents
- Included Involved Inspired A Framework for Youth Peer Education Programmes – IPPF (2007). https://www.ippf.org/sites/default/files/peer_education_framework.pdf
- Sexuality and Lifeskills Toolkit – Frontline AIDS (2019). https://frontlineaids.org/wp-content/uploads/2019/06/Sexuality-and-Life-skills-Toolkit.pdf
- Evidence-Based Guidelines for Youth Peer Education – FHI 360 (2010). https://www.fhi360.org/resource/evidence-based-guidelines-youth-peer-education
- Sexual, Reproductive Health and Life Skills for Youth Peer Education: a guide for trainers of facilitators – IFRC (2009). https://www.ifrc.org/Global/Publications/Health/youth_peer_education_EN.pdf
- Peer Education: Trainers Manual: Increasing the Knowledge and Skills of HIV-Positive Adolescents and Young Adults to Live Emotionally, Physically, and Sexually Healthy Lives – IAPAC (2014). https://www.iapac.org/support/peer-education/increasing-the-knowledge-and-skills-of-hiv-positive-adolescents-and-young-adults-to-live-emotionally-physically-and-sexually-healthy-lives/

# የአቻ ምክር




## ምሳሌ

እርጉዝ ለሆኑ ወይም ጨቅላ ሕፃናት ላሏቸው ወጣት ሴቶች ግሬሲ የእኩያ አማካሪ ነው ::ግሬሲም እንዲሁ እናት ስትሆን የ 2 ዓመት ልጅ አላት :: ግራሲ በአብዛኛው በማህበረሰቧ ውስጥ ትሰራለች እናም በቤት ውስጥ ወጣቶችን ስለ እርግዝና፣ ለወሊድ ስለመዘጋጀት፣  ስለ ለጡት ማጥባት እና ጡት ማስጣል ድጋፍ ታደርጋለች :: ለህጻናት ሊያስፈልጉ የሚችሉ እቃዎች ለምሳሌ እንደ ክሬሞች ፣ ብርድ ልብሶች እና ጠርሙሶች እንዲሁም ለወጣቶች ኮንዶሞች ማቅረብ ትችላለች  ::ግራሲ እንዲሁ እንደ የቤተሰብ ግንኙነቶች ፣ በቅርብ ግንኙነቶች ውስጥ የሚደርስን ጥቃት እና የአእምሮ ጤንነት ባሉ ሌሎች ጉዳዮች ላይም ድጋፍ ትሰጣለች :: በተጨማሪም ግሬሲ ከቤተሰብ አባላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶችን ትደግፋለች ::

ግራሲ ለወጣቶች የጤና ድጋፍ በሚሰጡ ባለሙያዎች የሰለጠነችና እና የተደገፈች ናት ::ለደንበኞቿ ግብረመልስ ትሰጣለች እናም ድጋፍ መጠየቅ ትችላለች ::ግራሲ ወጣቶችን ወደሚፈልጓቸው አገልግሎቶች ታስተላልፋቸዋለች ፣ ለምሳሌ የቤተሰብ እቅድ ምክር ፣ የአእምሮ ጤና ድጋፍ ፣ የ ስርዓተ ጾታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ፣ የአባላዘር በሽታ እና ኤች አይ ቪ ምርመራ አገልግሎቶችን ወደሚሰጡ አገልግሎት ሰጭወች ትመራለች። የህክምና ቀጠሮዎች ላይ እንዲገኙ ትደግፋቸዋል :: እሷም እናቶች ፣ ወጣት ወላጆች እና ሕፃናት የሚገናኙበት ፣ ሻይ የሚጠጡበት እና ነገሮች እንዴት እየሄዱ እንደሆነ የሚነጋገሩበትን ሳምንታዊ የማህበረሰብ ድጋፍ ቡድን ትመራለች ::ግራሲ አብራቸው ስለምትሰራቸው ወጣቶች ፣ ሕፃናት እና እድገታቸውንም በተመለከተ መዝገቦችን በመያዝ መረጃዎችን ትሰበስባለች

## ዓላማ

- ከራሳቸው ልምዶች በመነሳት ግለሰቦችን ወይም ትንንሽ ቡድኖችን መረጃዎችን በመስጠት ማማከር እና መምራት
- ተነሳሽነት ለማነሳሳት ፣ ለማበረታታት እና አርዓያ እንዲሆኑ ለማድረግ :: የአቻ አማካሪዎች እንዲሁ
- ስለ ድጋፍ እና አገልግሎቶችን መረጃን በመስጠት እና ተደራሽነት ላይ ድጋፍ ያደርጋሉ። በውሳኔዎች ዙሪያ ላይም ምክር ይለግሳሉ ::
- የአቻ አማካሪነት በአቻዎች የድጋፍ ሚና ላይ የተመሠረተ ነው። ይሁን እንጂ አማካሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በጤና አገልግሎት ወይም ስርዓት  እና በተወሰነ የጤና ጉዳዮች ውስጥ የበለጠ መረጃ እና ተሞክሮ ይኖራቸዋል

## አውድ/ሁነቶች

- የአቻዎች የማማከር አግልግሎት በማህበረሰብ ቦታዎች ማለትም ፣ በወጣት ክበባት ፣ በማህበራዊ ቦታዎች ፣ በእስር ቤቶች ወዘተ ውስጥ ይካሄዳል ::
- የማማከር ሂደት  መደበኛ (በአጠቃላይ ለተወሰነ የጊዜ የታቀደ) ወይም መደበኛ ያልሆነ ሊሆን ይችላል (ጥሩ ግንኙነቶችን በማሳደግ
- ቀስ በቀስ የሚያድግ) ማስተማሪያ ማስተዋወቂያ (ማስተዋወቂያ) ፣ የማማከር ሂደት መስታጋብራዊ እና በማመቻቸት ላይ የተመሰረተ ሲሆን መማር እና ልማት ለማሳደግ የታቀደ ሂደት ነው

## ጥቅሞች:

- የአቻ አማካሪዎች ከራሳቸው እና ከፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ተሞክሮ በመነሳት በእውቀት ላይ የተመሠረተ እና በራስ መተማመን የተሞላ ምክር እና መመሪያ መስጠት ይችላሉ ፡፡እነሱ ብዙውን ጊዜ ከአቻ ደጋፊዎች የበለጠ የላቀ የመረዳት እውቀት እንዳላቸው ተደርገው ይታያሉ ፣ እናም ጥልቀት ያለው መመሪያ ለመስጠት እና ችግሮችን በመፍታ ዙሪያ ሊረዱ ይችላሉ ፡፡
- የአቻዎች አማካሪዎች እንደ አርአያ ሆነው ያገለግላሉ እናም በፕሮግራሙ ተሳታፊዎች መካከል ተመሳሳይ ፍላጎትን ሊያሳድሩ ይችላሉ ፡፡
- የአቻ አማካሪነት  በተወሰነ የጊዜ ገደብ ለምሳሌ ለአንድ የተወሰነ ጊዜ ፕሮግራም ወይም ሂደት ውስጥ ሊተገበር ይችላል.
- የአቻ አማካሪ መርሃግብሮች በራስ መተማመን ፣ በራስ ውጤታማነት ላይ እና በማህበራዊ አውታረመረቦች ላይ በጎ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ

## ተግዳሮቶች / ውስንነቶች

- የአቻ አማካሪዎች ብዙውን ጊዜ መደበኛ በሆኑ የ 1 ለ 1 ግንኙነቶችን ያደርጋሉ። ይህም  ከባድ ጭነት/ወረፋ ሊያስከትል ይችላል።
- ሆኖም ፣ ከአቻ ደጋፊዎች በተለየ ፣ የእነሱ ሚና አብዛኛውን ጊዜ የሚቆየው ለተወሰነ ጊዜ ነው - ለምሳሌ  እንደ እርግዝና ባሉ ልዩ ክስተቶች ላይ ለአንድን ተሳታፊ ምክር መስጠት ፡፡
- በአቻ የማማከር ሂደት ውስጥ በሚፈጠረው ግንኙነቱ ውስጥ የኃይል ሚዛን መዛባት ሊፈጥር ይችላል ፣ ለምሳሌ አማካሪው ሁሉንም ነገር ይፈጽማል የሚል ግንዛቤ ካለ ፡፡የአቻዎች አማካሪዎች የተሰጡትን ምክሮች እና መመሪያዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የፕሮግራም ተሳታፊዎች የራሳቸውን ውሳኔ እንዲወስዱ ማበረታታት ያስፈልጋል ፡፡
- የአቻ አማካሪዎች በስርዓት ውስጥ መካተት እና ከሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ድጋፍ ማግኘት አለባቸው ፡፡
- የአቻ አማካሪዎች ሥራቸው ከግል ልምዳቸው ስለሚመነጭ የሙያ ድንበሮችን መጠበቅ መቻል አለባቸው

## አተገባበር

- በራስ መተማመን ያላቸውን እና ለሌሎች አዎንታዊ አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ የአቻ አማካሪዎችን ይምረጡ ፡፡የአቻ አማካሪዎች የበለጠ ልምድ ያላቸው እና ከአቻ ደጋፊዎች የበለጠ የግል ልምድ ያላቸው ናቸው። አማካሪዎች የበለጠ ተግባራዊ ምክር እና መመሪያ መስጠት መቻል እና በተገቢ ሁኔታ የመጠየቅ እና የመመርመር ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል።የአቻዎች ደጋፊዎች ደግሞ የበለጠ ስሜታዊ ድጋፍ ፣ ርህራሄ እና የምክር አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ ፡፡
- የአቻ ማማከር 1 ለ 1 ወይም በትንንሽ ቡድኖች ሊሰጥ ይችላል ፡፡ በቡድን ላይ የተመሠረተ የአማካሪ ፕሮግራሞች  በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶችን እና ወጣት ሴቶች የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ዕውቀትን እና ባህሪን በማሻሻል እና የኤች.አይ.ቪ ተጋላጭነትን በመቀነስ ዙሪያ ከ 1ለ 1 መርሃ ግብሮች የበለጠ ተፅእኖ አሳይተዋል ፡፡የቡድን የማማከር ሂደት በትምህርት ፣ በስኬት ፣ በገንዘብ አጠቃቀም ባህሪ እና የአመፅ ልምዶች በመቀነስ ረገድ መሻሻል አሳይቷል ፡፡

## ለበለጠ መረጃ ስልቶች እና ሃብቶች:


- Peer Mentoring for Health Behavior Change: A Systematic Review, R. L. Petosa & Dr Laureen H. Smith Pages 351-357. American Journal of Health Education (2014). https://eric.ed.gov/?id=EJ1044066

PLAN INTERNATIONAL

With support from Finland's development cooperation

በመጀመሪያ በ 2013 ታተመ

Text © ፕላን ኢንተርናሽናል 2013. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
የፕላን ኢንተርናሽናል ቅድመ ፈቃድ ሳይኖር የዚህ ጽሑፍ ክፍል በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ በኤሌክትሮኒክ ፣ በሜካኒካል ፣ በፎቶ ኮፒ ወይም በሌላ መንገድ ሊባዛ ወይም ሊተላለፍ አይችልም።

ፕላን ኢንተርናሽናል (2013). አቻን መሰረት ላደረጉ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብሮች መመሪያ. ዩናይትድ ኪንግደም፡ ፕላን ኢንተርናሽናል
ትርጉም በማህደር ተስፉ የሻው